# ትምህርት ፡ ፪

| | | |
|---|---|---|
| ተማሪ | |  |
|  | ተ | ተማሪ |
|  | ቱ | ቱባ Yarn |
|  | ቲ | ቲማቲም |
|  | ታ | ታኒካ Tin can |
|  | ቴ | ቴምብር stamp |
|  | ት | ትል tol |
|  | ቶ | ቶፋ tofa - small jar |





ይህ ፡ ተማሪ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ቱባ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ቲማቲም ፡ ነው ።
ይህ ፡ ታኒካ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ቴምብር ፡ ነው ።
ይህ ፡ ትል ፡ ነው ።
ይህ ፡ ቶፋ ፡ ነው ።

ያ ፡ ምንድር ፡ ነው ?
ያ ፡ ታኒካ ፡ ነው ።
ያ ፡ ምንድር ፡ ነው ?
ያ ፡ ቴምብር ፡ ነው ።
ይህ ፡ ማን ፡ ነው ?
ይህ ፡ ተማሪ ፡ ነው ።

## ትምህርት ፡ ፫

መቀስ



| | | |
|---|---|---|
|  | መ | መቀስ |
|  | ሙ | ሙዝ |
|  | ሚ | ሚዛን |
|  | ማ | ማር |
|  | ሜ | ሜዳ Field |
|  | ም | ምላስ Tongue |
|  | ሞ | ሞረድ mored File |



## ወዴት እዚህ እዚያ

ይህ ፡ መቀስ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ሙዝ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ሚዛን ፡ ነው ።
ይህ ፡ ማር ፡ ነው ።
ይህ ፡ ሜዳ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ምላስ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ሞረድ ፡ ነው ።

ያ ፡ ምንድር ፡ ነው ?
ያ ፡ ሙዝ ፡ ነው ።
ሚዛኑ ፡ ወዴት ፡ ነው ?
ሚዛኑ ፡ እዚህ ፡ ነው ።
መቀሱ ፡ ወዴት ፡ ነው ?
መቀሱ ፡ እዚያ ፡ ነው ።

## ትምህርት ፡ ፬

| | | |
|---|---|---|
| ለማኝ | |  |
|  | ለ | ለማኝ |
|  | ሉ | ሉክ Paper |
|  | ሊ | ሊጥ butter |
|  | ላ | ላባ |
|  | ሌ | ሌማት |
|  | ል | ልጅ |
|  | ሎ | ሎሚ |



አንድ　　　　አይደለም

ማን ፡ ነው ? ለማኝ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ሉክ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ሊጥ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ላባ ፡ ነው ።

ማን ፡ ነው ? አንድ ፡ ልጅ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ? ሎሚ ፡ ነው ፤

ይህ ፡ ሌማት ፡ ነው ? ሌማት ፡ አይደለም

I Dalem
It is not

ይህ ፡ ሉክ ፡ ነው ?

ይህ ፡ ሉክ ፡ አይደለም ።

ይህ ፡ ቴምብር ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሎሚ ፡ ነው ?

ይህ ፡ ሎሚ ፡ አይደለም ።

ይህ ፡ ሙዝ ፡ ነው ።

# ትምህርት ፡ ፮



የእኔ

| | | |
|---|---|---|
|  | የ | የእኔ |
|  | ዩ | እዩ |
|  | ያ | ያ |
|  | ይ | ይህ |
|  | ዮ | ዮሐንስ |



ይህ ፡ ቤት ፡ የማን ፡ ነው ?
ይህ ፡ ቤት ፡ የእኔ ፡ ነው ።
ያ ፡ በግ ፡ የማን ፡ ነው ?
ያ ፡ በግ ፡ የእኔ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ልጅ ፡ የማን ፡ ነው ?
ይህ ፡ የእኔ ፡ ልጅ ፡ ነው ።
እዩ ፤ ዮሐንስ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ቶፋ ፡ የእኔ ፡ ነው ?
የእኔ ፡ አይደለም ።
የለማኝ ፡ ቶፋ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ማር ፡ የእኔ ፡ ነው ?
የእኔ ፡ አይደለም ።
የዮሐንስ ፡ ማር ፡ ነው ።

# ትምህርት ፡ ፮

| | | |
|---|---|---|
| ረዥም | |  |
|  | ረ | ረዥም |
|  | ሩ | ሩቅ |
|  | ሪ | ሪዝ |
|  | ራ | ራስ |
|  | ሬ | ሬት |
|  | ር | ርግብ |
|  | ሮ | ጆሮ |



ትንሽ አንተ ናት

ይህ ፡ ልጅ ፡ ረዥም ፡ ነው ።
ይህ ፡ ቤት ፡ ሩቅ ፡ ነው ።
ይህ ፡ የለማኝ ፡ ሪዝ ፡ ነው ።
ይህ ፡ የልጅ ፡ ራስ ፡ ነው ።
ይህ ፡ መሬት ፡ የእኔ ፡ ነው ።
ይህች ፡ ርግብ ፡ ትንሽ ፡ ናት ።
ይህ ፡ የእኔ ፡ ጆሮ ፡ ነው ።

የአንተ ፡ ቤት ፡ ትንሽ ፡ ነው ?
የእኔ ፡ ቤት ፡ ትንሽ ፡ አይደለም ።
የአንተ ፡ ቤት ፡ ሩቅ ፡ ነው ?
የእኔ ፡ ቤት ፡ ሩቅ ፡ አይደለም ።
የአንተ ፡ ልጅ ፡ ረዥም ፡ ነው ?
የእኔ ፡ ልጅ ፡ ረዥም ፡ አይደለም ።



ይህ ፡ ልጅ ፡ ረዥም ፡ ነው ።



ይህ ፡ የማን ፡ ሪዝ ፡ ነው ?

ይህ ፡ የለማኝ ፡ ሪዝ ፡ ነው ።



ይህ ፡ የማን ፡ ራስ ፡ ነው ?

ይህ ፡ የተማሪ ፡ ራስ ፡ ነው ።

ያ ፡ ሌማት ፡ የማን ፡ ነው ?

ያ ፡ ሌማት ፡ የእኔ ፡ አይደለም ።

የዮሐንስ ፡ ሌማት ፡ ነው ።





ይህ ፡ የማን ፡ ቴምብር ፡ ነው ?

ይህ ፡ የዮሐንስ ፡ ቴምብር ፡ ነው ።



ይህ ፡  ፡ ነው ።



ይህ ፡  ፡ ነው ።

ይህ ፡  ፡ ነው ።



ይህ ፡  ፡ ነው ።

# ትምህርት ፡ ፯

| | | |
|---|---|---|
| ነብር | |  |
|  | ነ | ነብር |
|  | ኑ | ኑግ |
|  | ኒ | ጁኒያ |
|  | ና | እናት |
|  | ኔ | እኔ |
|  | ን | ንብ |
|  | ኖ | ኖራ Nora [illegible] |



አዎን መሬት አለ

ነብር ፡ እዚያ ፡ አለ ።
ኑግ ፡ እዚያ ፡ አለ ።
ጁኒያ ፡ እዚያ አለ ።
ንብ ፡ እዚህ ፡ አለ ።
ኖራ ፡ እዚህ ፡ አለ ።
የእኔ ፡ እናት ፡ እዚህ ፡ አለች ።

ማን ፡ ነው ? እኔ ፡ ነኝ ።
ነብር ፡ በሜዳ ፡ አለ ?
አዎን ፤ ነብር ፡ በሜዳ ፡ አለ ።
የዮሐንስ ፡ እናት ፡ እቤት ፡ አለች ?
አዎን ፤ እቤት ፡ አለች ።
ይህ ፡ መሬት ፡ የማን ፡ ነው ?
ይህ ፡ መሬት ፡ የእኔ ፡ ነው ።

# ትምህርት ፡ ፳

ወንድ



| | | |
|---|---|---|
|  | ወ | ወንድ |
|  | ዊ | ዳዊት |
|  | ዋ | ዋኘ |
|  | ው | ውሻ |
| ዎ | አዎን | |



## ስንት ዋጋ

ማን ፡ ነው ? ወንድ ፡ ልጅ ፡ ነው ።
ማን ፡ ነው ? ዳዊት ፡ ነው ።
ምንድር ፡ ነው ? ውሻ ፡ ነው ።
ይህ ፡ ተማሪ ፡ በባሕር ፡ ዋኘ ?
አዎን ፡ በባሕር ፡ ዋኘ ።

የቢላዋ ፡ ዋጋ ፡ ስንት ፡ ነው ?
የቢላዋ ፡ ዋጋ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ነው ።
የሎሚ ፡ ዋጋ ፡ ስንት ፡ ነው ?
የሎሚ ፡ ዋጋ ፡ ትንሽ ፡ ነው ።
የመሬት ፡ ዋጋ ፡ ትንሽ ፡ ነው ?
የመሬት ፡ ዋጋ ፡ ትንሽ ፡ አይደለም ።
የቤት ፡ ዋጋ ፡ ትንሽ ፡ ነው ?
የቤት ፡ ዋጋ ፡ ትንሽ ፡ አይደለም ።



በቤት ፡ ማን ፡ አለ ?

በቤት ፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አለ ?

አዎን ፡ ዳዊት ፡ በቤት ፡ አለ ።

ተማሪው ፡ በቤት ፡ አይደለም ።

ተማሪው ፡ በሜዳ ፡ አለ ።



የቶፋው ፡ ዋጋ ፡ ስንት ፡ ነው ?

ዋጋው ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ነው ።



በጆኒያው ፡ ምን ፡ አለ ?

ውሻው ፡ በጆኒያ ፡ አለ ።



ታኒካው ፡ ወዴት ፡ ነው ?

ታኒካው ፡ እዚያ ፡ ነው ።



ዋጋው ፡ ስንት ፡ ነው ?

ዋጋው ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ነው ።



በቤት ፡ ምን ፡ አለ ?



## ትምህርት ፡ ፱

| | | |
|---|---|---|
| ደወል | |  |
|  | ደ | ደወል |
|  | ዱ | ዱላ |
|  | ዲ | ዲዳ |
|  | ዳ | ዳቦ |
|  | ዴ | ስንዴ |
|  | ድ | ድመት |
|  | ዶ | ዶማ |



## ሁለት

ስንት ፡ ደወል ፡ አለ ? ሁለት ፡ አሉ ።
ስንት ፡ ዱላ ፡ አለ ? አንድ ፡ አለ ።
ስንት ፡ ዳቦ ፡ አለ ? አንድ ፡ አለ ።
ስንት ፡ ድመት ፡ አለ ? አንድ ፡ አለ ።
ስንት ፡ ዶማ ፡ አለ ? ፡ አንድ ፡ አለ ።
ስንዴ ፡ በቤት ፡ አለ ።
ያ ፡ ልጅ ፡ ዲዳ ፡ ነው ።

አንድ ፡ ሞረድ ፡ በቤት ፡ አለ ።
ሁለት ፡ ሞረዶች ፡ በቤት ፡ አሉ ።
አንድ ፡ ሁለት ።
አንድ ፡ ነብር ፡ በሜዳ ፡ አለ ።
ሁለት ፡ ነብሮች ፡ በሜዳ ፡ አሉ ።
ሁለት ፡ ቤቶች ፡ በሜዳ ፡ አሉ ።

## ትምህርት ፡ ፲

| | | |
|---|---|---|
| ሰው | |  |
|  | ሰ | ሰው |
|  | ሱ | ሱሪ |
|  | ሲ | ሲባጎ |
|  | ሳ | ሳሙና |
|  | ሴ | ሴት |
|  | ስ | ስኒ |
|  | ሶ | ምሰሶ |



## ወሰደ

ይህ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ወሰደ ?
ይህ ፡ ሰው ፡ ሱሪ ፡ ወሰደ ።
ያ ፡ ሰው ፡ ምን ፡ ወሰደ ?
ያ ፡ ሰው ፡ ሲባጎ ፡ ወሰደ ።
ይህች ፡ ሴት ፡ ምን ፡ ወሰደች ?
ይህች ፡ ሴት ፡ ሳሙና ፡ ወሰደች ።
ያች ፡ ሴት ፡ ምን ፡ ወሰደች ?
ያች ፡ ሴት ፡ ስኒ ፡ ወሰደች ።

ዳዊትና ፡ ዮሐንስ ፡ ምን ፡ ወሰዱ ?
ዳዊትና ፡ ዮሐንስ ፡ ዳቦ ፡ ወሰዱ ።
ሴቶች ፡ ምን ፡ ወሰዱ ?
ሴቶች ፡ ስንዴ ፡ ወሰዱ ።

# ትምህርት ፡ ፲፩

| | | |
|---|---|---|
| ገመድ |  | |
| ገ | ገ | ገመድ |
|  | ጉ | ጉጉት |
|  | ጊ | ጊንጥ |
|  | ጋ | ጋን |
|  | ጌ | ጌጥ |
|  | ግ | ግንድ |
|  | ጎ | ጎጆ |



ይህን ፡ ገመድ ፡ እዩ ።
ይህን ፡ ጉጉት ፡ እዩ ።
ይህን ፡ ጊንጥ ፡ እዩ ።
ይህን ፡ ጋን ፡ እዩ ።
ይህን ፡ ጌጥ ፡ እዩ ።
ይህን ፡ ግንድ ፡ እዩ ።
ይህን ፡ ጎጆ ፡ እዩ ።

ይህን ፡ ገመድ ፡ ውሰዱ ።
የእኔ ፡ አይደለም ። የሰው ፡ ነው ።
ይህን ፡ ጋኑ ፡ ውሰዱ ።
የእኔ ፡ አይደለም ። የተማሪ ፡ ነው ።
ይህን ፡ ልጅ ፡ እዩ ።
የእኔ ፡ ልጅ ፡ አይደለም ።



ይህ ፡ ገመድ ፡ የእኔ ፡ ነው ።

ገመዱ ፡ የአንተ ፡ አይደለም ።

አንድ ፡ ተማሪ ፡ ይህን ፡ ገመድ ፡ ወሰደ ።



ይህ ፡ ጋን ፡ የዳዊት ፡ እናት ፡ ጋን ፡ ነው ።

ጋኑ ፡ የእኔ ፡ አይደለም ።

አንድ ፡ ለማኝ ፡ ይህን ፡ ጋን ፡ ወሰደ ።



ይህ ፡ ሲባጎ ፡ የዮሐንስ ፡ ነው ።

ሲባጎው ፡ የዳዊት ፡ አይደለም ።

አንድ ፡ ተማሪ ፡ ይህን ፡ ሲባጎ ፡ ወሰደ ።

ተማሪው ፡ ይህን ፡ ሲባጎ ፡ ወሰደ ።



ይህ ፡ በግ ፡ የእኔ ፡ ነው ።

በጉ ፡ የአንተ ፡ አይደለም ።

አንድ ፡ ለማኝ ፡ ይህን ፡ በግ ፡ ወሰደ ።



ያ ፡ ተማሪ ፡ ማን ፡ ነው ?

ተማሪ☐ ፡ ዳዊት ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሰው ፡ ተማሪ ፡ ነው ።

ይህ ፡ ሰው ፡ ተማሪ ፡ አይደለም ።



ይህ ፡ ሰው ፡ ☐ ፡ ነው ።



ይህ ፡ ምንድር ፡ ነው ?

ይህ ፡ አንድ ፡ ትንሽ ፡ ቢላዋ ፡ ነው ።

የ☐ ፡ ዋጋ ፡ ስንት ፡ ነው ?

የ☐ ፡ ☐ ፡ አንድ ፡ ብር ፡ ነው ።

ዳዊት ፡ ይህንን ፡ ቢላዋ ፡ ወሰደ ።

☐ ፡ ቢላዋ ፡ ማን ፡ ☐ ?

ዳዊት ፡ ይህንን ፡ ቢላዋ ፡ ወሰደ ።

ይህ ፡ የማን ፡ ቢላዋ ፡ ነው ?

ይህ ፡ የዮሐንስ ፡ ቢላዋ ፡ አይደለም ።

የእኔ ፡ ቢላዋ ፡ አይደለም ።

ይህ ፡ የዳዊት ፡ ቢላዋ ፡ ነው ።

ዳዊት ፡ ይህንን ፡ ቢላዋ ፡ ወሰደ ።

## ትምህርት ፡ ፲፪

| ከበሮ | |  |
|---|---|---|
|  | ከ | ከበሮ |
|  | ኩ | ኩራዝ |
|  | ኪ | ኪስ |
|  | ካ | ካውያ |
|  | ኬ | ኬሻ |
|  | ክ | ክር |
|  | ኮ | ኮት |



ያ ፡ ከበሮ ፡ ነው ። ከበሮውን ፡ እዩ ።
ያ ፡ ካውያ ፡ ነው ። ካውያውን ፡ እዩ ።
ያ ፡ ኬሻ ፡ ነው ። ኬሻውን ፡ እዩ ።
ያ ፡ ኩራዝ ፡ ነው ። ኩራዙን ፡ እዩ ።
ያ ፡ ኪስ ፡ ነው ። ኪሱን ፡ እዩ ።
ያ ፡ ክር ፡ ነው ። ክሩን ፡ እዩ ።
ያ ፡ ኮት ፡ ነው ። ኮቱን ፡ እዩ ።

ኩራዙ ፡ ወዴት ፡ ነው ?
ልጁ ፡ ኩራዙን ፡ ወሰደ ።
ክሩ ፡ ወዴት ፡ ነው ?
እናቱ ፡ ክሩን ፡ ወሰደች ።
ካውያውን ፡ ማን ፡ ወሰደ ?
ተማሪው ፡ ካውያውን ፡ ወሰደ ።

ተማሪው ፡ ምን ፡ ወሰደ ?

፡ ፡ ።

---

በሜዳው ፡ ስንት ፡ በጎች ፡ አሉ ?

፡ ፡ ፡ አለ ።

---

በቤት ፡ ስንት ፡ ሰዎች ፡ አሉ ?

፡ አንድ ፡ ፡ አለ ።

---

ያ ፡ ምንድር ፡ ነው ?

| | |
|---|---|
| (1) ርግብ ፡ | (2) ______ |
| (3) ______ | (4) ______ |
| (5) ______ | (6) ______ |
| (7) ______ | (8) ______ |
| (9) ______ | (10) ______ |
| (11) ______ | (12) ______ |





# ትምህርት ፡ ፲፫

| | | |
|---|---|---|
| ሀብት |  | |
|  | ሀ | ሀብት |
|  | ሁ | ሁለት |
|  | ሃ | ሃያ |
|  | ሄ | ሄደ |
|  | ህ | አህያ |
|  | ሆ | ሆድ |



## ወደ

ይህ ፡ የሰው ፡ ሀብት ፡ ነው ።
ስንት ፡ ኮት ፡ አሉ ? ሁለት ፡ አሉ ።
ይህ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ሄደ ።
ይህ ፡ አህያ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ሄደ ።
ይህን ፡ ሆድ ፡ እዩ ።

ስንት ፡ ተማሪዎች ፡ አሉ ?
ሃያ ፡ ተማሪዎች ፡ አሉ ።
ማን ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሄደ ?
ያች ፡ ሴት ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሄደች ።
ልጁ ፡ ወዴት ፡ ሄደ ?
ልጁ ፡ ወደ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ሄደ ።
ዳዊትና ፡ ዮሐንስ ፡ ወዴት ፡ ሄዱ ?
ወደ ፡ ጎጆ ፡ ሄዱ

# ስድስት ሰባት ስምንት



ስንት ፡ ጆኒያዎች ፡ አሉ ?

ሁለት ፡ ጆኒያዎች ፡ አሉ ።



ስንት ፡ አህያዎች ፡ በሜዳው ፡ አሉ ? ሁለት ፡ አሉ ።



ስንት ፡ ታኒካዎች ፡ አሉ ?

ስድስት ፡ አሉ ።



ስንት ፡ ዱላዎች ፡ አሉ ?

ስምንት ፡ አሉ ።



ስንት ፡ ተማሪዎች ፡ አሉ ?

ሰባት ፡ አሉ ።



ስንት ፡ ሴቶች ፡ አሉ ?

አንድ ፡ ሴት ፡ አለች ።







## ትምህርት ፤ ፲፬

| | | |
|---|---|---|
| ጠረጴዛ | |  |
|  | ጠ | ጠረጴዛ |
|  | ጡ | ጡብ |
|  | ጢ | ጢም |
|  | ጣ | ጣት |
|  | ጤ | ጤፍ |
|  | ጥ | ጥርስ |
|  | ጦ | ጦር |



## ሰጠ

ይህ ፤ ሰው ፤ ጠረጴዛ ፤ ሰጠ ።
ይህ ፤ ሰው ፤ ጡብ ፤ ሰጠ ።
ይህ ፤ ሰው ፤ ጤፍ ፤ ሰጠ ።
ይህ ፤ ሰው ፤ ጦር ፤ ሰጠ ።
ይህ ፤ የሰው ፤ ጢም ፤ ነው ።
ይህ ፤ የሰው ፤ ጣት ፤ ነው ።
ይህ ፤ የሴት ፤ ጥርስ ፤ ነው ።

እናቱ ፤ ጤፍ ፤ ሰጠች ።
ለማን ፤ ሰጠች ? ለእኔ ፤ ሰጠች ።
ልጆች ፤ ጡብ ፤ ሰጡ ።
ለማን ፤ ሰጡ ? ለለማኝ ፤ ሰጡ ።
ዮሐንስ ፤ ኩራዙን ፤ ለዳዊት ፤ ሰጠ ።
ለማን ፤ ሰጠ ? ለዳዊት ፤ ሰጠ ።

## ትምህርት ፡ ፲፫

አበባ



| | | |
|---|---|---|
|  | አ | አበባ |
|  | ኢ | ኢትዮጵያ |
|  | ኤ | ኤሊ |
|  | እ | እጅ |
|  | ኦ | ኦሪት |



አበባ ፡ አለ ። አበባውን ፡ ውሰዱ ።
ያ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሄደ ።
አንድ ፡ ኤሊ ፡ አለ ። ኤሊውን ፡ እዩ ።
ይህ ፡ የማን ፡ እጅ ፡ ነው ?
የተማሪ ፡ እጅ ፡ ነው ።
ያ ፡ ሰው ፡ ኦሪት ፡ ሰጠ ።

እናቱ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሄደች ።
ልጆች ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ሄዱ ።
ልጁ ፡ ኮቱን ፡ ወሰደ ።
እናቱ ፡ ታኒካውን ፡ ወሰደች ።
ተማሪዎቹ ፡ ውሻውን ፡ ወሰዱ ።
ያች ፡ ሴት ፡ ሁለት ፡ ብር ፡ ሰጠች ።
ዮሐንስና ፡ ዳዊት ፡ ትንሽ ፡ ዳቦ ፡ ሰጡ ።

ሦስት አራት አምስት ዘጠኝ አሥር



አንድ ፡ ነብር ፡ በሜዳው ፡ አለ ።

ሁለት ፡ ተማሪዎች ፡ በጎጆ ፡ አሉ ።

ሦስት ፡ ውሻዎች ፡ እዚያ ፡ አሉ ።

አራት ፡ ሰዎች ፡ ገመዱን ፡ ወሰዱ ።

አምስት ፡ ሴቶች ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ሄዱ ።

ስድስት ፡ ድመቶች ፡ ወደ ፡ ሜዳው ፡ ሄዱ ።

ይህች ፡ ሴት ፡ ሰባት ፡ ጆኒያዎች ፡ ወሰደች ።

ስምንት ፡ ታኒካዎች ፡ ለእኔ ፡ ሰጠች ።

ዘጠኝ ፡ ብር ፡ እዚያ ፡ አለ ።

አሥር ፡ ርግቦች ፡ እዚያ ፡ አሉ ።



፩-1 አንድ ፡ ፪-2 ሁለት ፡ ፫-3 ሦስት

፬-4 አራት ፡ ፭-5 አምስት ፡ ፮-6 ስድስት

፯-7 ሰባት ፡ ፰-8 ስምንት

፱-9 ዘጠኝ ፡ ፲-10 አሥር




(አሁን ፡ 124 ፡ ቃላት ፡ ተምርሃል ።)

